ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
<u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!
እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡
የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡
በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
<u>ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር አድርሳ የምትኖረው ኢትዮጵያ
የመሲሓችን እናትና የእኛም እናት፣
የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች
ንግሥት፡ እግዝእተብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት።

---

**ቍጥር ፲፮/፳፻፱ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ ወእምነ፥ ወሀገሪትነ ወሃይማኖትነ፥ ወመድኃኒትነ ወንግሥትነ፡
ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ ወፈጣሪነ፥ ወአምላክነ ወካህንነ፥ ወሰላምነ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።

ማለትም፡-

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እግዝእተብሔር እናታችንና አገራችን፥
ሃይማኖታችንና መድኃኒታችን፥ ንግሥታችንም በኾነችው፡
አምላክን በወለደችው፡
በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በመለኮትነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፥
እግዚአብሔር ወልድና ፈጣሪያችን፥ አምላካችንና ካህናችን፥ ንጉሣችንና ሰላማችንም በኾነው፡
በኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ \+ \+

## ይድረስ፡-

በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥
በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥
በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡
የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፥

ስሜ በተጠራባት፡ በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁትና
በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥
በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥
በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥

ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡
የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡
"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡
በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፥

በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡
የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡
ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ!

እንዲሁም፡
የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡
በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፥
ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥
በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!

በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬ፡ ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

# መቅድም

እንዳለፈው፡ እንደ፲፫ኛውና ከእርሱ እንደቀደሙት ተከታታይ መለኮታውያት የዐዋጅ ቃሎቼ ኹሉ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዝእተብሔር እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመ-ቤታችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ**።

## የዚህ ዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ ምክንያት፡

ለዚህ፡ ለአኹኑ የዐዋጅ ቃሌ፡ መነሻ የኾነው ምክንያት፡ ምን እንደኾነ፡ አስቀድሜ ልንገራችሁ! ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡-

በግዝረት ምልክትነት የተገለጠውንና ጸንቶ የኖረውን ኪዳነ-አብርሃምን፤ እንዲሁም፡ የሕፃን ኢየሱስ መሲሕን ግዝረት፤ የእናንተንም ግዝረት፤ ከዚህም ጋር፡ እኔን፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን በእጮኛነት፥ ልጄን ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕንም፡ ከፅንሰቱና ከልደቱ፥ በጠቅላላም፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ፡ በፍጹም ቅንነትና ታማኝነት ያገለገለንን፡ ባለሟላችንን፡ ጻድቁ ዮሴፍን፥ በዚህ ተልእኮ፡ ከእርሱ ያልተለየችውን፡ የቅርብ አገልጋያችንን፡ ሰሎሜን ጭምር በሚመለከት፤

በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ ታውቃና ታምኖባት የኖረች፡ ማንኛውም ዓይነት ተቃዋሚ ኃይል፡ መንፈሳዊዉም ኾነ፥ ሥጋዊው፡ በተቃዋሚነት፡ ሊቋቋማት፤ በተፃራሪነትም ሊያስወግዳት ያልቻለ፥ የማይችልም፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር እውነት አለች።

ነገር ግን፡ በዚህ ረገድ ያለችው፡ <u>ይህችው፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር እውነት፡</u> ልጄን ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን እስከመግደል በደረሰ ጥላቻና ተቃውሞ፡ እስከዛሬ እያሳደዱት ባሉት፡ በአይሁድ ዘንድ፡ ለ፫ሺ፱ ዓመታት፥ ይልቁንም፡ ግብረ-ዐበሮቻቸው በኾኑት፡ በግብፅ ኦርቶዶክሳውያን መነኮሳት ደግሞ፡ ለ፩ሺ፮፻፱ ዓመታት፤

"ኢትዮጵያዊ ነኝ!" እያለ፡ በስሜ ከሚጠራው፡ ከዚህ፡ ከከሃዲውና ከዓመፀኛው፥ ከአመንዛሪውና ከክፉው ትውልዴ ዘንድ፡ እንዲህ፡ በሓሰቱ አበጋዝ፡ በዲያብሎስና በአገልጋዮቹ የክፋት ሠራዊት፡ ተዳፍናና ተገልላ እንድትኖር በመደረጉ፡ እነሆ፡ ለረዥም ዘመናት፡ ተደብቃና ተሠውራ፥ ማስናና ምስጢር ኾና፡ ሳትከሠት ቆይታለች።

ዛሬ ግን፡ በዚህ ረገድ ያለችውን፡ <u>ይህችኑ፡ የእኛ የኾነችውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡</u> ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በንጉሥነቱ፥ እኔም፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ በንግሥትነቴ፡ በገሃድ እና በቀጥታ በምንመራት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን አማካይነት፡ እኔው ራሴ፡ በዚህ፡ የዐዋጅ ቃሌ፡ ይፋ አውጥቼ፡ ለመላዎቹ ፍጡሮቻችን፥ በተለይም፡ በቅዱሱ ኪዳን ላገኘኋችሁ፡ ለእናንተ፡ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት፡ የቃል ኪዳን ልጆቼ፡ ልገልጽላችሁ የሚያስፈልግ ኾኖ በመገኘቱ፡ ይኸው፡ ስለዚችው <u>የእግዚአብሔርን እውነት፡</u> እያናገርኋችሁ አለሁ፤ እናንተም፡ እነሆ፡ እየሰማችሁኝ አላችሁ።

## በግዝረት ምልክትነት የተገለጠውና ጸንቶ የኖረው ኪዳነ-አብርሃም።

የቅዱሱ ኪዳን አካል ከኾኑት፡ ከሰባቱ አባላት፡ አንዱ ስለኾነው፡ "ኪዳነ-አብርሃም" ስለሚባለው፡ ስለግርዛት፡ በተለይ፡ በመስከረም ፰ ቀን የሚውለውን፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ የግዝረቱን ዓመታዊ መታሰቢያ ቀን በምታዘክሩበትና በምታከብሩበት የበዓል ሰሞን፡ ይህን መለኮታዊ እና ትስብእታዊ ግዝረትን የሚመለከተውን እግዚአብሔራዊ እውነታ፡ እንድታውቁት የማድረጉ ተግባር አስፈላጊና ተገቢ ኾነ።

በመኾኑም፡ ታላቅ ቊም-ነገርን የተላበሰው፡ ይኸው፡ የመንፈስ ቅዱስ ዕውቀት፡ እንደተለመደው፡ በእኔው የዐዋጅ ቃል፡ እነሆ፡ ይፋ እንዲወጣላችሁ ተደረገ።

ካለፉት ቃላተ ዐዋድ መካከል፡ በአንዳንዶቹ ውስጥ፡ ስለዚሁ፡ ስለልጄ-ወዳጄ ግርዛት፡ ቀደም ብዬ፡ በጥቂቱ የጠቀስሁላችሁ ብኾንም፡ አኹን ግን፡ ስለእርሱም ኾነ፡ በእርሱ ዙርያ ስላሉት ተዛማጅ ቊም-ነገሮች ጭምር፡ በክፉዎች ሰዎች በኩል፡ ምሥጢራት ተደርገውባችሁ ስለቆዩት፡ ስለሌሎቹ የእግዚአብሔር እውነቶች ሳደርግላችሁ እንደቆየሁት ኹሉ፡ አኹን፡ ደግሞ፡ ስለዚሁ ስለግርዛት፡ ሰፋ ባለ መልክ እና ይዘት፡ የመንፈስ-ቅዱሳዊው ዕውቀት ባለቤቶች ትኾኑ ዘንድ፡ በእናትነቴ፡ ኹሉንም፡ በዚሁ የመንፈስ-ቅዱስ፡ የዕውቀት ብርሃን፡ በበለጠ ግልጽ ላደርግላችሁ ፈለግሁ። ስለዚህም፡ ከዚህ እንደሚከተለው አቀረብሁላችሁ፡-

# የኢየሱስ መሲሕ ግዝረት።

በቅዱሳት መጻሕፍታችሁ: "ወአመ ተፈጸመ ሰሙን ዕለት፡ ወሰድዎ ለሕፃን፡ ከመ ይግዝርዎ፤ ወሰመይዎ ስሞ፡ 'ኢየሱስ!' በከመ ሰመዮ መልአክ፡ እምቅድመ ትፅንሶ በከርሣ።

"[የዐራስነቱ] ስምንተኛ ቀን እንዳበቃ፡ ሕፃኑን ይገርዙት ዘንድ፡ ወሰዱት፤ [ድንግሊቱ እናት] እርሱን፡ በማሕፀኗ ከመፅነሷ በፊት፡ መልአክ እንደሰየመው፡ ስሙን፡ 'ኢየሱስ!' ብለው ሰየሙት።" ተብሎ እንደተጻፈው፡ ይህ ቃል፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የኦሪቱን ሥርዓት እንደፈጸመ ለማስቆጠር ያህል፡ ወደመግረዣው ቦታ የወሰድነው መኾናችንን ብቻ የሚያስረዳ ከመኾኑ በቀር፡ "ወሰድዎ፤ ...ወሰመይዎ ስሞ፡ 'ኢየሱስ!'፣ ወሰዱት፤ ...ስሙንም፡ 'ኢየሱስ!' ብለው ሰየሙት!" እንዳለው ኹሉ፡ ነገር ግን፡ <u>'ገዘርዎ! ገረዙት' ባለማለቱ፡ በሰውኛው መልክና ይዘት፡ በሥጋው ተገርዞ ደም እንዳልፈሰሰው፡ አረጋግጦ አሳውቋል።</u> (ሉቃ. ፪፥ ፳፩።)

የልጄ የወዳጄ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ መለኮታዊው የትስብእት ደሙ፡ የመጨረሻው አማናዊው የፋሲካ በግ ኾኖ፡ በመስቀል ላይ፡ በቤዛነት ታርዶ፡ የኃጢኣት ማስተስረያ፥ የክፋቱ ጦርነት ድል አድራጊና የዘለዓለማዊቷ ሰላም አስገኚ ተጋዳይ፥ በሞቱ፡ የሞት ደምሳሽና የትንሣኤ ብኵር ኾኖ፡ ደሙ የሚፈስሰውና የፈሰሰው፡ ገና በዕለተ ዓርብ፡ መጋቢት ፳፱ ቀን፥ ፴፫ ዓመተ-ምሕረት በመኾኑ ነው።

ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ገና በማሕፀኔ፡ በትስብእታዊው ሥጋ ሲፀነስ፡ ራሱን፡ ለዚህ ቤዛነት ያዘጋጀ በመኾኑ፡ <u>በተፈጥሮው ግዙር [የተገረዘ]፥</u> በዚህ ብቻ ሳይኾን፡ <u>በወንድነቱም፡ ሕጽው [ጃንደረባ]</u> እንደኾነ ልታውቁት ይገባል። ይህንም የእግዚአብሔር እውነት፡ ከዚህ ከቀደሙት፡ የዐዋጅ ቃሎቼ፡ በአንደኛው እንደገለጽሁላችሁ ታስታውሳላችሁ።

ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በእኔ፡ በእናቱ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም አማካይነት እና የዓለም መድኃኒትነት፡ በሰውነት ተፀንሶና ተወልዶ የመጣው፡ ለምን እንደኾነ፡ በተለይ፡ እናንተ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ ዐውቃችሁት የለምን? በእርግጥ፡ ዐውቃችሁታል።

አዎን! ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከጠንቀኛው ተቃዋሚ፡ ከዲያብሎስና በእርሱ አበጋዝነት ከሚመሩት፡ ከክፋቱ ሠራዊት አንፃር፡ ቀድሞ፡ በመለኮቱ፥ ኋላም፡ በትስብእቱ፡ በነፍስና በሥጋ፡ በመንፈስም ሲያካኺደው ከኖረውና ማብቂያ ካልነበረው የዝንተ-ዓለም ጦርነት፡ በቤዛነት ተጋድሎውና ሞቱ፡ ይህንኑ ባለጋራውንና የጦር ኃይላቱን፡ ፈጽሞ ድል አድርጓል።

ድል አድርጎም፡ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ! ሥርዉ ለዳዊት!"፥ "የዳዊት ሥር የኾነው፡ የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!" በተባለበት፡ በዚህ ድሉ፡ ዘለዓለማዊዉን ሰላም፡ ለፍጡሩ ሰው እና ለፍጥረተ-ዓለማቱ አስገኝቶ፡ ይህንኑ ያስገኘውን፡ ፍጹሙን ሰላሙን፡ ይኸው፡ ለዚሁ ለፍጡሩ ሰው እና ለፍጥረተ-ዓለማቱ አስጨብጦአል።

የልጁ የወዳጁ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በሰውነት፡ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱ ብቸኛ ዓላማ፡ ይህ በመኾኑ፡ የግዙርነቱና የጃንደረብነቱ አስፈላጊነትና ተገቢነት፥ ትክክለኛነትና እውንነት፡ በተለይ በመነሻ ዓላማነቱ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ የመጨረሻው የድል አድራጊነት ግቡ በኾነው፡ በሰላም አስገኝነቱ ጭምር ተረጋግጦላችኋል።

## የ፩፻፵፬ሺ ሕፃናት የመሥዋዕትነት ደም፡<br>በሄሮድስ እጅ እንዲፈስስ፡ ለምን አስፈለገ?

የእኔን፡ የድንግል ማርያምን ብቅዓት፡ ምክንያት አድርጎ፡ የእርሱን፡ የልጄን የወዳጄን የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ትስብእት [ሰው መኾን] ያስከተለው፡ የሰው ልጆች ክፋት፥ ኃጢአትና በደል፡ በኖኅ እና በሎጥ ጊዜ ከነበረው ይልቅ፡ እጅግ በዝቶ፥ ጽዋው ሞልቶና ተርፎም፡ እየፈሰሰ ኼዶ፡ እንኳንስ የሚታየው ግዙፉ ሥጋና ሥጋዊዉ ፍጥረት ቀርቶ፡ የማትታየው፡ ረቂቋ ነፍስና ነፍሳዊው ፍጥረት ጭምር፡ ፈጽመው ከመጥፋቱና ከመደምሰሱ የገደል አፋፍ ደርሰው እንደነበረ፡ አኹን አሳውቃችሁ ዘንድ አስፈላጊ ኾኗል።

ይኹን እንጂ፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የቤዛነት ደሙን፡ በሕማማተ-መስቀሉ ጊዜ አፍስሶ፡ ከፍጥረታተ-ዓለማቱ በፊት ጀምሮ፡ በመለኮትነቱም፥ በትስብእትነቱም፡ ሲዋጋው የኖረውን፡ ዲያብሎስንና ሠራዊቱን፡ በድል አድራጊነቱ አሸንፎ፡ ዘለዓለማዊቷን ሰላም መልሶ እስኪመሠርት ድረስ፤

አዎን! ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእኔ ከተወለደባት አፍታ አንሥቶ፡ በመጨረሻ፡ በመስቀል ላይ ደሙን አፍስሶ፡ ክፋትን፡ በደግነት፥ ሐሰትን፡ በእውነት፤ ያም ማለት፡ ኃጢአትን፤ በጽድቅ፥ ሞትንም፡ በሞቱ ደምስሶና አጥፍቶ እስኪያስወግድ ድረስ፡ ባለው ክፍት ጊዜ ውስጥ፡ ሊያጥለቀልቅ አቆብቁቦ የነበረውን የጥፋቱን ማዕበል ገድቦ ለማቆየት፡ ምን ዓይነት መሥዋዕትነትን መክፈል ያስፈለገን ኾኖ የተገኘ መሰላችሁ? ከጥቂቶች በቀር፡ ብዙዎቻችሁ፡ በዚህ ረገድ ያለችውን፡ ይህችን የእኛን፡ መለኮታዊ እውነት ለማወቅ ተስኗችሁ ኖርዋል።

ጨካኙና ግፈኛው፡ ይሁዲው ሄሮድስ፡ ልጄን ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ ለመግደል ሲል፡ ያስፈጃቸው፡ የእነዚያ፡ የ፩፻፵፬ሺ [አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ] ሕፃናት፡ ፍጹም ንጹሕ ደም፡ በሰማዕትነት እንዲሠዋ፡ በእርግጥ አስፈለገ!

እነዚያ ሕፃናት፡ እስከዚያ፡ እስከልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሲሕ መስቀለ-ሞት ድረስ ላለው ጊዜ፡ ለፍጥረታተ-ዓለማቱ፡ ቤዛ ኾነው፡ ፍጹም ንጹሕ ደማቸው እንዲፈስስ ተደረገ። አዎን! ተሠዉ። የእነርሱ ዝክረ-ነገር እውነታው፡ ይህ ነው።

እነዚህ ሕፃናት፡ ዛሬ ስለሚኖሩበት ሕይወት፡ ልጇ ዮሓንስ፡ በራእዩ ስላየው እውነታ፡ እንዲህ የሚለውን፡ መንፈሳዊዉን የሰማይ ቃል ጽፎላችሁ፡ እያነበባችሁት አይደለምን? አዎን! እያነበባችሁት ነው። እስኪ! አኹንም፡ እንደገና ስሙት!

***"ወእምዝ ቆመ፡ ዝክቱ በግዕ፡ ላዕለ ደብረ-ጽዮን፤ ወምስሌሁ፡ ፲ወ፬፼ወ፵፬ (ዐሠርቱ ወአርባዕቱ እልፍ ወአርባ ምእት) እለ ጽሑፍ ውስተ ፍጽሞሙ፡ ስሙ፥ ወስመ አቡሁ፥ ወስመ ቅዱስ መንፈሱ።***

***"ወመጽአ ቃል እምሰማይ፡ ከመ ቃለ ማይ ብዙኅ፤ ወከመ ቃለ ነጐድጓድ ዐቢይ፤ ወከመ ቃለ መሰናቁት፣ ሶበ ይሰነቅዉ፡ በበመሰንቆታቲሆሙ። ወየኀልዩ፡ ማኅሌተ፡ ሐዲሰ፡ ቅድመ-መንበሩ፣ ወቅድመ እልክቱ፡ አርባዕቱ እንስሳሁ፤ ወእልክቱኒ ሊቃናት።***

***"ወአልቦ ዘይክል አእምሮታ፡ ለይእቲ ማኅሌት፣ ዘእንበለ እልክቱ ፲ወ፬፼ወ፵፬ እለ ተቤዘዉ እምነ ምድረ-ግብፅ። እለ ንጹሓን እሙንቱ፡ እምአንስት፣ በከመ ተወልዱ እሙንቱ፤ እለ ተለውዎ ለበግዑ፡ ኀበ ሖረ፤ እለ ቀደሙ ተቤዝዎ፡ እምነ እጓለ-እመሕያው፡ ለእግዚአብሔር፥ ወለበግዑ። ወኢተረክበ ሓሰት፡ ውስተ አፉሆሙ፤ እስመ ንጹሓን እሙንቱ እምኃጢአት።***

"ከዚህ በኋላ፡ ይኸው በግ፡ በጽዮን ተራራ ላይ ቆመ። ከእርሱም ጋር፡ በእየግንባራቸው ላይ፡ ስሙ፥ የአባቱ ስም እና የቅዱስ-መንፈሱ ስም የተጻፈባቸው፡ ፲፬፼፵፬ (*ዐሥራ-አራት እልፍ አራት ሽህ=አንድ መቶ አርባ አራት ሽህ*) ነበሩ።

"እንደብዙ ውኃ ድምፅ፥ እንደታላቅ የነጐድጓድም ድምፅ፥ ባለመሰንቆዎች፡ መሰንቆዎቻቸውን በሚቃኙበት ጊዜ፡ እንደሚያሰሙት ዓይነት ድምፅ፡ ከሰማይ ቃል መጣ፤ በዙፋኑ ፊት፥ በእኒህ፡ በአራቱ እንስሳትና በእኒሁ ሊቃናት ፊት፡ አዲስ የዝማሬ ማሕሌትን አሸበሸቡ።

"ይህችንም ማሕሌት፡ ከእነዚሁ፡ የግብፅን ምድር ከተቤዡት ከ፲፬፼፵፬ዎቹ (ከመቶ አርባ አራት ሽህዎቹ) በቀር፡ የሚያውቃት የለም። ከእናቶቻቸው ማሕፀን ነጽተው እንደወጡ፡ በጉን ወደኼደበት የተከተሉት። ከሰው ልጆች መካከል፡ ለእግዚአብሔር እና ለበጉ ሲሉ፡ በቅድሚያ ቤዛ ኾነው የተሠዉ። በአንደበታቸው፡ ሓሰት አልተገኘባቸውም፤ ከኃጢአት የነጹ ናቸውና። (ራእ. ፲፬፥ ፩-፭።)

## የግርዛት ቃል ኪዳን፡
## በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ።

"ኪዳነ-አብርሃም" የምትሉት፡ ግርዛት፣ "ጵላተ-ኪዳን" እና "ታቦተ-ጽዮን" እንደምትሏት፡ እንደ"ኪዳነ-ሙሴ"፥ እንደ"ኪዳነ-ዳዊት"ም ኹሉ፡ ከእኛ ከእግዚአብሔር፡ ለእስራኤል ልጆች የተሰጠ፡ የመጀመሪያው ቃል-ኪዳን ምልክት እንጂ፡ የእኔ፡ የኢትዮጵያ ልጆቼ ለኾናችሁት፡ ለእናንተ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የተሰጠ አይደለም። ይህን፡ ታውቁ ኖርዋል? ካወቃችሁት፡ መልካም፤ ካላወቃችሁት ግን፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እንድታውቁት ይኹን!

የእስራኤል ልጆች፡ ስለአምልኮተ-እግዚአብሔር፡ ከማእከላዊው፡ ኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ ተምሮ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት አማኝ ለመኾን በበቃው፡ በአብርሃም አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን፡ የግርዛት ቃል-ኪዳን፤ እግዚአብሔር በሚቀበለው፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ መፈጸም ስለአቃታቸው፡ እንደኪዳነ-ሙሴና እንደኪዳነ-ዳዊት ኹሉ፡ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ የኪዳነ-አብርሃም ምልክት የኾነውን ግርዛትንም፡ ከሃይማኖቱና ከምግባሩ ጋር፡ በባለአደራነትና በእውነተኛ አምላኪነት የተቀበሉት እንጂ፡ ሥጋዊው የአብርሃም ግርዛት፡ ምንጊዜም ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸው ኾኖ አይደለም።

እነርሱ፡ እኒሁ የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ ነፍሳዊዉንና መንፈሳዊዉን ግርዛት፡ ጥንቱኑ በፍጥረታቸው፥ ቀደምም ብለው፡ በሃይማኖታዊው ምግባራቸው፡ ፈጽመውት የኖሩ፥ ሲፈጽሙትም የሚኖሩ በመኾናቸው፡ ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸው አልኾነም።

"የአብርሃም ልጆች ነን!" በሚሉት፡ በአይሁድ ዘንድ ያለው የኦሪቱ ሕግ፡ የግርዛቱን ቃል ኪዳን፡ በዕድሜው ሸምግሎ ከነበረው፡ ከራሱ፡ ከአብርሃም ጀምሮ፡ ወንድ የኾነው ሕፃን ብቻና ኹሉ፡ በተወለደ፡ በ፰(ስምንት)ኛው ቀን እንዲፈጽም የሚያዝዝ ሲኾን፡ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ ግን፡ አምላካዊው የግርዛቱ ትእዛዝ፡ እየተፈጸመ እንዲጠበቅ የተደረገው፡ <u>በወንዶቹ ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በሴቶቹም ዘንድ እንዲኾን መደረጉን፡</u> ኹላችሁም፥ ሌላውም ኹሉ የሚያውቀው ነው።

ይህ ሥርዓታዊ ምግባር፡ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ፡ እንዲህ፡ ጸንቶ እንዲቀጥል በመደረጉ፡ በዚህ፡ እግዚአብሔራዊ ቃል ኪዳን ጭምር፡ እኒሁ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ የእኛን የፈጣሪያቸውን ቃል ኪዳናዊ ትእዛዝ፡ ሳይቀንሱም፥ ሳይጨምሩም፡ በእውነትና በትክክል፡ ጠብቀው የሚፈጽሙ ለመኾናቸው፡ ሌላው ምስክር ነው።

መቸም፡ በእኛ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም ፍጡሮቻችንና ልጆቻችን፡ በተፈጥሮ ያቀዳጀናቸው የእኩልነት መብትና የሥልጣን ደረጃ፡ በምንም መልክና ይዘት፡ ፈጽሞ ሊገሠሥ እንደማይቻል፡ በሌሎች ዘንድ ቢቀር፡ በኢትዮጵያ ልጆቻችን ዘንድ፡ ያለእንከን ይታወቃል።

ይህ እውነታ፡ እንዲህ፡ በእርግጠኛነት እየታወቀ፡ ነገር ግን፡ ይህን የግርዛትን የቃል ኪዳን መለኮታዊ ትእዛዝ፡ እኛ እግዚአብሔር፡ ለወንዶች ፍጡሮቻችን ብቻ እንደሰጠነው ተደርጎ፡ "የአብርሃም ልጆች ነን!" በሚሉ፡ በአይሁድ ዘንድ፡ እንዴት ሊነገርና ሊጻፍ እንደተቻለ፣ እንደተደፈረም ለማወቅ፡ ለማንም፡ ይህን ያህል አዳጋች አይኾንም። ምክንያቱም፡ እነርሱ፡ የእኛ፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ኹሉ፡ ምንጊዜም፡ ከመቃወምና ከመለወጥ፥ ከማጣመምና ከማማሰን የማያርፉ፥ የማይሰንፉም መኾናቸው፡ አእምሮ ባላቸው ፍጡሮቻችን ዘንድ፡ በይፋ ስለሚታወቅ ነው።

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን ግን፡ በእነዚሁ ዕብራውያን አይሁድ፡ "ተነገረ! ተጻፈ!" የተባለው፥ ይህ መለኮታዊ የኾነው፡ የግርዛት ቃል ኪዳን ትእዛዝ፡ በባለአደራነት፡ ወደእነርሱ እንዲተላለፍ በተደረገበት ጊዜ፡ ትክክለኛውንና አማናዊዉን የሥርዓቱን አፈጻጸም ዐውቀውት እንዴት፡ ሴቶች ሕፃናት ልጆቻቸውን ጭምር፡ በስምንተኛው ቀን የሚገርዙ ኾኑ? ይህ ለምንና እንዴት ሊኾን ቻለ?

እኒህ፡ በቅዱሱ ኪዳን ታማኞቻችን የኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ "አባግዕየሰ፡ እሊአየ ይሰምዓኒ ቃልየ፤ ወአነሂ አአምሮን፤ ወይተልዋኒ። ወአነሂ እሁቦን ሕይወተ ዘለዓለም። ወኢይትሐጐላ ለዓለም። ወአልቦ ዘየሃይደኒዮን እምእዴየ።

"የእኔ የኾኑት በጎቼማ፡ ቃሌን ይሰማሉ፤ እኔም ዐውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኛማል። እኔም፡ የዘለዓለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘለዓለምም አይጠፉም፤ ከእጄም፡ የሚነጥቃቸው የለም።" ያላቸው በመኾናቸው ነው። (ዮሐ. ፲፥ ፳፯-፳፰።)

ከዚህ የተነሣ፡ በቅዱሱ ኪዳን ታማኞቻችን የኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ የእኛ የኾነውን፡ ድምፃችንንና ቃላችንን፥ ትእዛዛችንንና ሥርዓታችንን በመላው፡ ጥሩ አድርገውና ለይተው ያውቁታል፤ ሰምተውና ተቀብለው፥ ዐውቀውና አምነው የሚከተሉትም፡ ምንጊዜም፡ ያን፡ የእኛ የኾነውን ኹሉ ነው።

ለዚህ ነው፡ የግርዛቱን ቃል ኪዳን፡ በባለአደራነት ተቀብለው፡ በሃይማኖታዊነቱና በምግባራዊነቱ ጭምር በሚፈጽሙበት ጊዜ፡ ያን፡ የአብርሃምንና የመሰሎቹን የጣዖት አምልኮ ኃጢአት፡ ወንዶቹ ብቻ ሳይኾኑ፡ ሴቶቹም ጭምር የፈጸሙት በመኾኑ፡ "የእኛም ደም፡ መፍሰስ አስፈላጊ ነው!" በማለት፡ ሴቶቹ ሕፃናት ልጆቹ ጭምር፡ ትርፍ እንደኾነው፡ እንደወንዶቹ ሸለፈት ዓይነት፡ በሴቶቹም አፈ-ማሕፀን፡ ትርፍ የኾነውን ሥጋ ብቻ፡ ለምልክትና ደም ለማፍሰስ ያህል፡ እንዲገረዙት ያደረጉት።

በዚህም፡ ከእኛ፡ በተፈጥሮ በተሰጣቸው፡ መለኮታዊ ሥልጣን፡ በእኩልነት በተቀዳጁት የልጅነት መብታቸው፡ የቃል ኪዳኑ በረከት ተሳታፊዎች መኾናቸውን ብቻ ሳይኾን፣ የአብርሃም ሴቶች ልጆች፡ ሊቀበሉት የሚገባቸውን፡ የቅጣቱንም ጠንቅ፡ ዋጋ ከፋዮች መኾናቸውን ጭምር አረጋግጠዋል።

## አይሁድ፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት አፍራሽነታቸው።

በቅዱሱ ኪዳን ታማኞቻችን የኾኑት፡ እኒሁ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ በዚህ ረገድ፡ ይህን የመሰለውን፡ የአብርሃምን ሃይማኖታዊ ምግባር ሲፈጽሙ፡ እኛ፡ ይህን የግርዛት የቃል ኪዳን መለኮታዊ ትእዛዝ፡ ለወንዶች ብቻ እንደሰጠነው ተደርጎ፡ "የአብርሃም ልጆች ነን!" በሚሉ በአይሁድ ዘንድ፡ እንዴት ሊነገር፣ ሊጻፍስ እንደተቻለ፣ እንደተደፈረም፡ ልጁ ወዳጁ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ይህንኑ በሚመለከት፡ ከዚሁ ከግርዛት ጋር አያይዞ፡ ለእነዚሁ ለተቃዋሚዎቹ አይሁድ የተናገረውን ቃል፡ እስኪ ስሙት!

"ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ፤ ወይቤሎሙ፡- '...ለምንት እንከ፡ ተኀሥሡ ትቅትሉኒ? ...አሐደ ግብረ ገበርኩ፤ ወኵልክሙ አንከርክሙ። በእንተ ዝንቱ ወሀበክሙ ሙሴ፡ ግዝረተ፤ ወኢኮነት እምኀበ ሙሴ፤ አላ፡ እምአበው ይእቲ።

"ወበሰንበት ትገዝርዎ ለሰብእ። ወእመሰ በሰንበት፡ ግዝረተ ይነሥእ ብእሲ፡ ከመ ኢይሰዐር ሕጉ ለሙሴ፡ ለምንት እንከ ትግእዙኒ፡ ለእመ አሕየውክዎ ለብእሲ ኵለንታሁ በሰንበት? ኢትፍትሑ በአድልዎ ለገጽ፤ አላ፡ ፍትሐ-ጽድቀ ፍትሑ!

"ፈጣሪያችን ኢየሱስም መለሰላቸው፤ አላቸውም፡- '...እንግዲያ፡ ለምን ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ? እኔ፡ አንድ ሥራ በማደርግበት ጊዜ ኹሉ፡ እናንተ፡ ያንን ታደንቃላችሁ። ለዚህም፡ የሙሴ ሥራ ማስረጃ ይኹናችሁ! ሙሴ፡ ግዝረትን ሰጣችሁ፤ እርሷም፡ ከቀደሙ አባቶች የተሰጠች እንጂ፡ ከሙሴ የኾነች አይደለችም።

"በሰንበትም፡ ሰውን ትገርዛላችሁ። እንግዴህ፡ ['ሰንበትን አክብር!' የሚለውን፡ ታላቁንና ቀዳሚዉን፥ የመጀመሪያ የኾነውንም፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት፡ እንዲህ በመተላለፍ፤ ነገር ግን፡] የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ብላችሁ፡ ሰው፡ በሰንበት፡ ግዝረትን እንዲቀበል የፈቀዳችሁ ከኾነ፡ ታዲያ! እኔ፡ በሰንበት፡ ሰውን፡ ኹለንተናውን፡ [ከሕመሙ ፈውሼ፡] ፍጹም ጤናማ ስላደረግሁት፡ ለምን፡ እንዳጠፋሁ ቆጥራችሁ፡ በእኔ ላይ ትቆጣላችሁ? እውነተኛ ፍርድን ፍረዱ እንጂ፡ ለምን [ኢትዮጵያዊ] መልኬን አይታችሁ፡ በፍርዳችሁ፡ አድልዎን ትፈጽሙብኛላችሁ?" (ዮሐ. ፯፥ ፳፱-፳፫።)

ልጁ ወዳጁን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ከመግደል ያልተመለሱት፡ እኒሁ አይሁድ፡ ሙሴ፡ በሠራላቸው ኦሪታዊ ሕጋቸው ምክንያት፡ የእኛን እግዚአብሔራዊ ሥርዓት የማፍረሳቸው ድፍረት የተለመደ እንጂ፡ እንግዳ አለመኾኑን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የዚህኑ ልጁ ወዳጁን፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ሌላውን ተመሳሳይ ቃሉን ደግሞ፡ እስኪ ስሙት!

ይኸውም፡ እኛ እግዚአብሔር አብ እና እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እርሱን፡ አንድ ቅዱስ ልጃችንን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በመለኮትነትም፥ በትስብእትነትም ልንወልደው፥ እንዲሁም፡ አንድ ቅዱስ መንፈሳችንን እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስንም፡ በመለኮትነትም፥ በመንፈስነትም ልናሠርፀው፡ የሠራነውን፡ ሕያው እና ዘለዓለማዊ፥ መለኮታዊ እና ሰብአዊ የኾነውን፡ የጋብቻን ሥርዓት የሚመለከተው ነው።

ከዚያ በመነሣት፡ እነዚሁ አይሁድ ፈሪሳውያን፡ ልጇ ወዳጇን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በጥያቄያቸው ሊፈታተኑትና አጥምደው ሊጥሉት፡ "ይከውኖሁ ለብእሲ፡ ይድኃር ብእሲቶ፡ በኵሉ፡ ዘአበሰት ሎቱ?

"ባል፡ ሚስቱ፡ በምታደርስበት በማናቸውም በደል ምክንያት ኹሉ፡ ሊፈታት ይፈቀድለታልን?" ብለው በጠየቁት ጊዜ፡ የመለሰላቸው፡- "ኢያንበብክሙኑ፡ ዘውስተ ኦሪት፡ ከመ ዘፈጠሮሙ እግዚአብሔር እምትካት፡ ተባዕተ፥ ወአንስተ ገብሮሙ? በእንተዝ፡ የኀድግ ብእሲ፡ አባሁ፥ ወእሞ፤ ወይተልዋ ለብእሲቱ፤ <u>ወይከውኑ ክልኤሆሙ፡ አሐደ ሥጋ። እንከሰኬ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ፡ አሐዱ ሥጋ እሙንቱ። ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፣ ሰብእ ኢይፍልጥ!</u>

"እግዚአብሔር፡ ጥንት፡ ከመጀመሪያው፡ ወንድ እና ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸው፡ በኦሪት የተጻፈውን አላነበባችሁምን? ስለዚህ፡ ወንድ፡ አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ሚስቱንም ይከተላታል፤ <u>ኹለቱም፡ አንድ ሥጋ ይኾናሉ። ከእንግዲህ ወዲህ፡ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፡ ኹለት አይደሉም። እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ በጋብቻ አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው!"</u> ብሎ እንደነበረ ይታወሳል።

እነርሱም፡ መልሰው፡- "ለምንት አዘዘ ሙሴ፡ የሀቡ መጽሐፈ ፍልጣን! ወይኅድግዋ!

"ታዲያ! ለምን፡ ሙሴ፡ 'ባልዬው፡ የፍቺዋን ጽሑፍ ሰጥቶ፡ ሚስቱን ያሰናብታት!' ብሎ አዘዘ?' ሲሉ፡ እንደገና ጠየቁት።

እርሱም፡- <u>"ሙሴሰ አዘዘክሙ፡ በከመ እከየ ልብክሙ፣ ከመ ትኅድጉ አንስቲያክሙ፤ ወበቀዳሚ ፍጥረትሰ፡ አኮ ከማሁ።</u> እብለክሙ አነሂ፡ 'ኵሉ ዘይድኅር ብእሲቶ፡ ዘእንበለ ትዘሙ በላዕሌሁ፣ ለሊሁ፡ ረሰያ፡ ዘማ፤ ወእንተሂ ደኅርዋ አውሰበ፡ ዘመወ!'

<u>"ሙሴማ፡ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ፡ ይህን ትእዛዝ የሰጣችሁ፡ በየልባችሁ ክፋት ምክንያት ነው። በፍጥረት መጀመሪያ ግን፡ እንዲህ አይደለም።</u> እኔም እላችኋለሁ፡- 'ሚስቱ፡ በላዩ ካልሴሰነችበት በቀር፡ [እርሱም፡ በእርሷ ላይ ካልሴሰነ በቀር] ሊፋቱ አይገባም! አለዚያ፡ እርሱ፡ እርሷን፡ አመንዝራ ያደርጋታል፤ እንዲህ የተፈታችውን ያገባም፡ ራሱን፡ አመንዝራ ያደርጋል። እርሷም፡ እርሱን፡ አመንዝራ ታደርገዋለች፤ እንዲህ የፈታውን ያገባችም፡ ራሷን፡ አመንዝራ ታደርጋለች።" አላቸው።

ይህን በመሰለው፡ በአይሁድ ተፃራሪ አስተሳሰብና ድርጊት፡ የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ደቀ-መዛሙርት ሳይቀሩ እንደተባበሩ፡ ከዚያ፡ ከፈሪሳውያኑ አይሁድ ጥያቄና መልስ የቀጠለውን ንግግር፡ ይኸው ተከታተሉት!

"ወይቤልዎ አርዳኢሁ፡- 'እመሰ፡ ከመዝ ውእቱ ሥርዓተ ብእሲ ወብእሲት፡ ኢርቱዕ ያውስቡ!'

"ደቀ-መዛሙርቱም አሉት፡- 'የባልና ሚስት ሥርዓት፡ እንዲህ ከኾነ፡ ጋብቻ፡ በትክክል ሊኖሩት የሚቻል አይደለም።'

"ወይቤሎሙ፡- 'አኮ ኵሉ ዘይክሎ፡ ለዝንቱ ነገር፡ ዘእንበለ ዳእሙ ዘተውህቦ። እስመ ቦ ሕፅዋን፡ እለ ከማሁ ተወልዱ እምከርሠ እሞሙ፤ ወቦ ሕፅዋን፡ እለ ሓፀውዎሙ ሰብእ፤ ወቦ ሕፅዋን፡ እለ ሐፀዉ ርእሶሙ፡ በእንተ መንግሥተ-ሰማያት። ወዘሰ ይክል ተዓግሦ፡ ለይትዓገሥ።'

"እርሱም አላቸው፡- 'አዎን! ያለጋብቻ፡ ሊኖሩ ይቻላቸው ዘንድ፡ [ከሰማይ] የተሰጣቸው ካልኾኑት በቀር፡ ይህ [የጋብቻ ኑሮ] ነገር፡ ለኹሉ የሚቻል አይደለም። እነርሱም፡ ገና፡ በእናቶቻቸው ማሕፀን ሣሉ፡ ጃንደረቦች ኾነው፡ እንዲህ የሚወለዱ አሉና። አረማዊም የሰለባቸው፡ ጃንደረቦች አሉ፤ ስለመንግሥተ-ሰማያት ሲሉም፡ [አባለ-ዘራቸውን ሰልበው]፡ እየራሳቸውን ጃንደረባ ያደረጉ አሉ። በዚህ ጃንደረብነት፡ እስከመጨረሻው ጸንቶ ለመኖር የሚችል፡ ይጽና!'" (ማቴ. ፲፱፥ ፲-፲፪።)

## የአብርሃም ግርዛት ለምን አስፈለገ?

አብርሃም፡ የሥጋ ግርዛት ያስፈለገው፡ ያለምክንያት አልነበረም። ቀድሞ፡ በጣዖት አምላኪነቱ ጊዜ፡ ያው ዲያብሎስ ላደረበት ጣዖቱ ይሠዋ የነበረው፡ የእንስሳትን፥ ወይም፡ የአዕዋፋትን ደመ-ነፍስና ሥጋ ብቻ ሳይኾን፣ በይበልጥ፡ ሰዎች የኾኑትን፡ ወንዶች፥ በተለይም ሴቶች ልጆቻቸውን እያረዱ፡ ደማቸውን በማፍሰስ ይፈጽሙ እንደነበሩት፡ እንደወገኖቹ ኹሉ እንደነበረ፡ በኹላችሁም ዘንድ ይታወቃል።

ኋላም፡ "ወበደም ይነጽሕ ኵሉ፡ በሕገ-ኦሪት፤ ወዘእንበለ ይትነዛኀሰ ደም፡ ኢይሠረይ።

"በኦሪቱ ሕግ፡ ኹሉ የሚነጻው፡ በደም ነው፤ ደም ሳይረጭማ [ሳይፈስስማ] ስርየት የለም።" እየተባለ፡ በዕብራውያን ሥርዓት እንደሚደረገው ኹሉ፡ ይህን በመሰለ፡ የአምልኮ ደም የተፈጸመ ታላቅ ኃጢአት፡ የሚሰረየው፡ በዚያው፡ በደም ኾኖ ቀጠለ። (ዕብ. ፱፥ ፳፪።)

ስለዚህ፡ ታማኙ ኢትዮጵያዊ ባለሟል ካህናችንና አጼያችን፡ መልከ-ጼዴቅ፡ ለአብርሃም፡ ስለእኛ፡ ስለእግዚአብሔር እና ስለአምልኳችን ሥርዓት፡ በሚበቃ ስላሳውቀው፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት ተረድቶና ተገንዝቦ ካመነ በኋላ፡ ያ ኹሉ፡ የእርሱና እርሱን የመሰሉት ኹሉ፡ የኃጢአታቸው ክምችት፡ ለአንዴና፥ ለዘለዓለም የሚሰረይበት [የሚወገድበት]፡ የልጇ የወዳጇ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ደም፡ በመስቀል ላይ በቤዛነት እስኪፈስስ ድረስ፡ እርሱን፡ አብርሃምንና እርሱን የመሰሉትን ኹሉ፡ በተስፋ አጽንቶ፥ ለመጨረሻው የምሕረት ቃል ኪዳን ያበቃቸው ዘንድ፡ ሊያቆያቸው የቻለውን፡ የግርዛቱን ቃል ኪዳን፡ አብርሃምም፥ ዘሮቹም እየፈጸሙ ይጠብቁት ዘንድ ግድ ኾነ።

አዎን! ግድ የኾነውም፡ ዲያብሎስ፡ ሰዎችን፡ ከእግዚአብሔር አምልኮ አስክዶ፡ በጣዖቱ አማካይነት፡ እርሱን፡ [ዲያብሎስን] እንዲያመልኩት ሲያደርግ፥ ሲያስደርግም የኖረው፡ የሰዎችን፡ የወንዶችንም ኾነ የሴቶችን ደም፡ በመሥዋዕትነት በማስፈሰስ እንደመኾኑ፣ አኹንም፡ ያ ታላቅ ኃጢአት፡ ለጊዜውም ቢኾን፡ እየተሰረየ ሊቆይ የሚችለው፥ የሚገባውም፡ በዚያው፡ በሰው ደም መኾኑ፡ አግባብና ፍትሕ ርትዕ በመኾኑ፣ ከራሱ ከአብርሃም ጀምሮ፥ የእርሱ የኾኑት፥ የኋላ ዘሮቹ ሳይቀሩ፥ ኹሉም ወንዶች፡ የአባለ-ዘር ሸለፈታቸውን፥ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ ግን፡ ሴቶች ጭምር፡ የአፈ-ማሕፀናቸውን ትርፍ ሥጋ በመገረዝ፡ ደማቸው እንዲፈስስ፡ የግድ አስፈላጊ ኾነ። የግርዛት ደም እንዲፈስስ፡ አስፈላጊና ተገቢ የኾነበት አስገዳጁ ምክንያት፡ ይኼ ነው።

## <u>የእኔ እጮኛ ኾኖ ስላገለገለው፡ ስለጻድቁ ዮሴፍ።</u>

ሕፃን ልጇ ወዳጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከማሕፀን ጀምሮ፡ በተፈጥሮው፡ <u>ግዙር [የተገረዘ] እና ሕጽው [ጃንደረባ]</u> መኾኑን ገልጨላችኋለሁ።

ይህ ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ ከተነሣ ዘንድ፡ በቍም-ነገር ሊወሳ የሚገባው፡ ሌላም፡ ሊገለጥ የሚገባው፡ ተዛማጅ እውነታ አለ። ያም እውነታ፡ ከዚያን ከፅንሰቱ ጊዜ አንሥተው ያልተለዩኝ፡ የደጉ ኢትዮጵያዊ አገልጋያችን፡ የጻድቁ ዮሴፍ እና የደጊቱ ኢትዮጵያዊት አገልጋያችን የጻድቂቱ ሰሎሜ፡ በዚህ ረገድ፡ ከዚሁ ጋር፡ ተያይዞ ያለው የማንነታቸውና የምንነታቸው ዝክረ-ነገር፡ እዚህ ላይ፡ ዐብሮ ሊነገር የሚገባው ኾኖ ተገኝቷል።

አዎን! እኛ እግዚአብሔር፡ የማይታዩትንም ኾነ፥ የሚታዩትን ፍጥረታተ-ዓለማት፡ ከመፍጠራችን በፊትም ኾነ፥ ከፈጠርናቸው በኋላ፡ ስለኾነውና ስለሚኾነው፥ ስለመነሻው እና ስለመንደርደሪያው ኹሉ፥ የመጨረሻ ግብ ኾኖ የተጠበቀውን፣ ዘለዓለማዊዉን ሕይወት ስላስከተለውም፡ <u>ስለዘመነ ሥጋዌ፡</u> እስኪ፡ ለጥቂት አፍታ፡ በተመሥጦ አስቡ!

በአንድ በኩል፡ የዚህን የዘመነ ሥጋዌን፡ ፍጹም ብቅዓትና ዝግጁነት፡ እኛ እግዚአብሔር፡ አስቀድመን ማወቅ ብቻ ሳይኾን፡ የኩነቱም ባለቤቶች በመኾናችን፡ ስለእርሱ የተናገርነው ቃል፥ የተካየድነው ኪዳን፥ የሰጠነው ተስፋ፥ ያስነገርነው ትንቢት፥ ያስቆጠርነው ሱባዔ፣ ያሳየነው ራእይ፥ ያስተረጐምነውም ሕልም፡ ጊዜው ደርሶ፡ ይህን ኹሉ መለኮታዊ እና ትስብእታዊ ትንግርት፡ በምድር ላይ፡ በሰዎች መካከል፡ እውን አድርገን፡ በእየራሳችን ላይ የምንገልጥበትና የምንፈጽምበት፡ ይህ፡ የእኔ፡ የእግዝእተብሔርዋ እም ድንግል ማርያም እናትነት እና የልጄ የወዳጄ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ሕፃንነት አለ።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ ይህን መለኮታዊ እና ትስብእታዊ እናትነትና ሕፃንነት፡ በምድር ላይ፡ በግዘፍ ሰውነት እንዲያገለግሉ የተጠሩ፥ እየራሳቸውንም ለዚህ የተልእኮ ጥሪ አብቅተው የተገኙ፡ ጻድቁ ዮሴፍ እና ጻድቂቱ ሰሎሜ አሉ።

ታዲያ! የእኒህ ኹለት ሰብኣት ፍጡሮቻችን ምንነትና ማንነት፡ ለእናንተ፡ በምን ዓይነት መጽሔት ተገልጦ፥ እንዴትስ ባለ መሥፈርት ላይ ተቀምጦ ነው፡ ሊከሠትላችሁ፥ ሊመዘንላችሁም የሚገባው ይመስላችኋል?

ከእናንተ፡ እንደአንዳችሁ፡ "ታማኞች ልጆቻችን" ብዬ በመጥራት ብቻ ላመልክታቸውን? ስለእኒህ ኹለት፡ የተመረጡ ሰብኣት አገልጋዮቻችን፥ በተለይም፡ ስለጻድቁ ዮሴፍ፡ በሰዎች ዘንድ፡ ስንትና ምን እየተባለ እንደተኖረ፥ አኹንም ድረስ፡ ምን እንደሚባል፡ ኹላችሁ የምታውቁት አይደለምን? አዎን ታውቁታላችሁ። ያን የሰዎች ይትበሃል፡ ያን ላሉት፡ ለእነርሱው፡ ለእየራሳቸው ትቼ፡ እኔ፡ የእኛ የእግዚአብሔር የኾነውን እውነት ብቻ እነግራችኋለሁ።

ለዚህ እውነታ፡ መሠረትና መነሻ የማደርገው፡ የእናንተኑ የቅዱሳት መጻሕፍታችሁን ቃላት ነው። ከእነዚህም መካከል፡ ለዓይነት ያህል፡ አንዱን፥ ይኸውም፡ በብሥራተ-ማቴዎስ ሓዋርያ፡ "**መጽሐፈ ልደቱ፡ ለእግዚእነ ኢየሱስ መሲሕ።**

"የእግዚአብሔራችን የኢየሱስ መሲሕ፡ የልደቱ መጽሐፍ" በሚል መግቢያ የሚጀምረውንና፡ እንዲህ የሚለውን ብቻ ልጥቀስላችሁ፡- "**ከመዝ ውእቱ ልደቱ፡- ወሶበ <u>ተፍኅረት</u> እሙ ማርያም፡ ለዮሴፍ፡ ዘእንበለ ይትቃረቡ፡ ተረክበት ፅንስተ፡ እመንፈስ ቅዱስ። ወዮሴፍሰ፡ <u>ፈኃሪሃ</u>፡ <u>እስመ ጻድቅ ውእቱ</u>፣ ኢፈቀደ ይክሥታ፤ ወመከረ፡ ጽሚተ፡ ይኅድጋ።**

"ልደቱም፡ እንዲህ ነው፡- እናቱ ማርያም፡ ለዮሴፍ <u>ታጭታ</u> ሣለ፡ ሩካቤ-ሥጋ ሳያደርጉ፡ ከመንፈስ ቅዱስ፡ ፅንሳ ተገኘች። <u>እጮኛዋ</u> ዮሴፍ ግን፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ነውና፡ ሊያጋልጣት አልፈለገም፤ በነገሩ፡ አውጥቶ አውርዶ ካሰበበት በኋላ፡ በሥውር ሊተዋት ወሰነ። (ማቴ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፲፰።)

## እጮኛነት፤
## የባልና ሚስት መተጫጨትም ሥርዓት።

እንግዴህ፡ በወዳጇ በጻድቁ ዮሴፍ እና በእኔ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም መካከል ያለው ግንኙነት፡ በእጮኛነት ደረጃ መኾኑን፡ የእግዚአብሔሩ እውነትና የቅዱሳት መጻሕፍቱ ቃላት፡ እንዲህ በግልጽ አረጋግጠውታል።

የእጮኛነትን ዝክረ-ነገር በሚመለከት ደግሞ፡ ከጥንት፣ ከመሠረቱ፣ ከአዳም እና ከሔዋን የፍጥረት ጊዜ ጀምሮ፡ እስከዛሬው ዘመናችሁም ድረስ እንኳ ቢኾን፡ ጸንቶ ሲሠራበት የኖረና ያለ፡ የባልና ሚስት መተጫጨት ሥርዓት እንዳለ ታውቃላችሁ።

ያም፡ ሥርዓት፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ እኛ እግዚአብሔር አብ እና እግዝእተብሔር እም፡ አንድ ቅዱስ ልጃችንን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በመለኮትነትም፥ በትስብእትነትም ልንወልደው፥ ደግሞም፡ አንድ ቅዱስ መንፈሳችንን፡ እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስን፡ በመለኮትነትም፥ በመንፈስነትም ልናሠርፀው፡ የሠራነውን፡ ሕያው እና ዘለዓለማዊ፥ መለኮታዊ እና ሰብአዊ የኾነውን፡ የጋብቻን ሥርዓት በፈጸምንበት ጊዜ፥ እኛም፡ አስቀድመን ያካኼድነው፥ እንዲሁም፡ ጋብቻን የሚፈጽሙ ሰዎች ፍጡሮቻችን ኹሉ እንዲፈጽሙት የሠራንላቸው፥ የሚያስፈልጋቸውም ኾኖ ሲያደርጉት የኖሩና አኹንም የሚያደርጉት የመተጫጨት ሥርዓት ነው። ከዚያ የሚቀድመው፡ የሽምግልና ሥርዓትም እኮ አለ። ለዚያም፡ ባለምሥራቹን፡ ሊቀ-መላእክታችንን፡ ገብርኤልን አስቡት!

አዎን! በዚህ የመተጫጨት ሥርዓት መሠረት፡ ለእግዚአብሔራዊው ሥርዓተ-ጋብቻ አፈጻጸም፡ በወንዱ በኩል፡ ለሚስትነት የሚያጫት፡ አንዲት ሴት፡ "ድንግል" መኾን እንደሚገባት ኹሉ፣ በሴቷም በኩል፡ እንዲሁ፡ እርሱን፡ ለባልነት የምታጨው ወንዱም፡ ድንግል መኾን እንዳለበት፡ በማንኛችሁም ዘንድ ተቀባይነትና ተፈጻሚነት ያለው፡ እውነታ ነው።

ይህ ሥርዓት፡ ከማንም በበለጠ፡ ዕውቅናንና ተፈጻሚነትን አግኝቶ፡ በእናንተ፡ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ እንደኖረ፣ አኹንም፡ እየሠራ እንደሚገኝ አያጠያይቅም።

ስለዚህ ነገር፡ እንኳንስ፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ተቀብላችሁና ጠብቃችሁ፣ አክብራችሁና አጽንታችሁ በመኖር ረገድ፣ በዚህም ማንነታችሁና ምንነታችሁ፡ በፍጥረተ-ዓለሙ ዘንድ፡ በስመ-ጥሩነት በታወቃችሁት፣ ከዚህ የተነሣም፡ ቀድሞ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!" ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" ልትባሉ በበቃችሁት፡ በእናንተ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ ቀርቶ፡ በሌሎች፡ "ጨዋና ሥልጡን" በተባሉ ሕዝቦችና አሕዛብ ዘንድ እንኳ፡ እንደሚደረግ ይታወቃል።

አዎን! ገሃዱ ኹኔታ፡ ይህ ኾኖ ሣለ፥ አኹን እየተሠራበት ያለው እውነታም፡ ይኸው፡ የሥርዓቱ ዘይቤ ከኾነ፡ ታዲያ! ለምንና እንዴት ነው፡ ለጻድቁ ዮሴፍ ብቻ፡ ይህ የወል ጸጋና መብት፡ በሰዎች ዘንድ የተነፈገው?

እርሱ፡ ጻድቁ ዮሴፍም እኮ፡ እናንተ፡ "የእኔ-ብጤ" የምትሉት፡ ተራ ሰው አይደለም፤ ለእኔ፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ "እጮኛ" ኾኖ፥ ለዚህ፡ የአንድ ጊዜ ብቻ፥ ታላቅና ብርቅ፥ መለኮታዊና ትስብእታዊ ተልእኮ [አገልግሎት]፡ ራሱን አብቅቶ፥ እርሱም፡ እንደእኔ፡ በድንግልናው ጸንቶ በመገኘቱ፡ በእኛ ተመርጦና ተጠርቶ የተሠየመ ነው።

መቸም፡ እናንተም ሰዎች ስለኾናችሁ፣ በእርሱ ላይ ብቻ በደረሰበት፡ በዚሁ፡ ክፉዎች ሰዎች በፈጸሙበት፡ በንፍገቱና በአድልዎው በደል ውስጥ፡ እናንተ ጭምር ተካፋዮች ኾናችሁ ልትገኙ ስለምትችሉ፡ በዚህ ረገድ ለቀረበው፡ ለዚህ ጥያቄ፡ ተገቢውንና ትክክለኛውን መልስ፡ እናንተም ልትሰጡ ይገባችኋል።

ለኹሉ የተሰጠው፡ ይህ የወል ጸጋና መብት፡ በሰዎች ዘንድ፥ በይበልጥም፡ በእነዚያ፡ በአይሁድና እነርሱን በመሰሉት ኹሉ ዘንድ፡ ለእርሱ፡ ለታማኙ ጻድቅ እጮኛዬ፡ ለዮሴፍ ብቻ ስለተነፈገውማ፡ ዝርዝሩን፡ እናንተም በምታውቁት መጠን፡ ስለእርሱ የኾነውንና እየኾነ ያለውን፥ የተባለውንና እየተባለ ያለውንም ኹሉ፡ አምኖ ለመቀበል፡ ለማንኛችሁም እንደሚከብዳችሁ ግልጽ ኾኖ፡ ይኸው፡ በየጎሊናችሁ ፊት ያለማቋረጥ እየመሰከረባችሁ እንደቀጠለ ይገኛል።

በእኔ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በእርሱ፡ በጻድቁ ዮሴፍ መካከል ያለው፡ በንጽሕና የተቀደሰውና አፍአዊ የኾነው የእጮኛነት ግንኙነት፡ ፍጹም እግዚአብሔራዊ በመኾኑ፡ በባሕርዩ፡ ሊማስንላቸው አልቻለም እንጂ፡ እነዚሁ ሰዎች፡ በሰይጣናዊው የክፋትና በሰውኛው የጥፋት ዓቅማቸውማ፡ ኾን ብለው በፈጠሩት ስሑት [የሓሰት] ውዝግባቸው ምክንያት፡ በእየራሳቸው መከከል፡ ምን ያህል የጠለቀና ጠንቀኛ የኾነ፡ የሃይማኖት መለያየትን ፈጥረው፣ የልጆቻችንን ህልውና፡ ይኸው፡ ለከባድና ለውስብስብ ችግር ዳርገውት፡ እነሆ፡ ኹሉም፡ መፍትሔ በሌለው፡ ጽኑ ፈተናና መከራ እንደሚሠቃዩ ትመለከቱታላችሁ። ይህ ብቻ ሳይኾን፥ "ክርስቲያን ነን!" የሚሉት፡ እኒሁ፡ የእኛ የምንላቸው የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፡ እስከዛሬና ዛሬም፡ ወደእርስ በርስ መጠላላትና የደም መፋሰስ ገደል እስከመውደቅ፥ ወደጦርነትና የዕልቂት አዘቅት ውስጥም እስከመዘፈቅ ደርሰው፡ አኹንም ገና በመማቀቅ ላይ እንደሚገኙ፡ ይኸው ውጤቱን፡ እየራሳችሁ፡ በየፊናችሁና በጋራም እያያችሁት ነው።

ይህን የመሰለው፡ አሳዛኝና አሠቃቂ ኹኔታ፡ እንዲህ ደርሶ የሚታየው፡ የእናንተ፡ የኹላችሁ ልጆቻችን ሕይወት፡ በመጀመሪያ፡ እኔ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ በማዳኔ መሥዋዕትነት፤ በመጨረሻም፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በሰላም ቤዛነቱ፥ ለዘለዓለማዊው ፍጹም መልካምነት ያበቃነው መኾኑ በተረጋገጠበት፡ የምሥራቹና የምሕረቱ ዘመናችን በመኾኑ፡ ኹኔታውን፡ በእናንተው ዘንድ፡ የበለጠ አሳዛኝ ብቻ ሳይኾን፣ አስገራሚም አድርጎታል። ይኸው ውጤት፡ እንደተለመደው፡ የ"ሰዎች የክፋት ዝንባሌ፡ ያስከተለው መራራ ፍሬ ነው!" ከማለት በስተቀር፡ አሳማኝ የኾነ፡ ሌላ በቂ ምክንያት፡ ከቶ የምታገኙለት አይደለም።

## ሰዎች ሊያማስኑት የሞከሩት፡
## ቅዱሱ እጮኛማነት።

*ታዲያ! ከዚህ የተነሣ አይደለም እንዴ!፡-*

-አይሁድ እና እነርሱን የመሰሉት ኹሉ፡ "ማርያም፡ እንደማንኛዪቱም ሴት፡ የዮሴፍ ሚስቱ ኾና፡ ድንግልናዋን ከተገሠሠች በኋላ፡ ከዚሁ፡ ከባልዋ፡ ከዮሴፍ፡ የበኵር ልጃቸው የኾነውን፡ ኢየሱስን እና ሌሎች፡ ወንዶችን፥ ሴቶችንም ልጆች ወልደዋል!" የሚሉት!?

-"ክርስቲያን ነን!" የሚሉት ፀረ-ማርያሞች ደግሞ፡ "ማርያም፡ በድንግልናዋ እያለች፡ ከመንፈስ ቅዱስ፡ የመጀመሪያ ልጇን፡ ኢየሱስ መሲሕን ፀንሳ ካረገዘችና ከወለደች በኋላ፡ ከዚሁ፡ ከባልዋ፡ ከዮሴፍ፡ ሌሎች፡ ወንዶችንና ሴቶችን ልጆች ወልዳለታለች!" የሚሉት!?

-እንደእነዚያ ኹሉ፡ "ከፀረ-ማርያሞቹ ይልቅ፡ እንዲያውም፡ ቀደምቶቹ ክርስቲያኖች፡ እኛ ነን!" የሚሉት፡ ኦርቶዶክሳውያንና ካቶሊካውያንም፡ "የለም! ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚያ በድንግልናዋ ጸንታ እያለች፡ በ፲፭ ዓመቷ፡ ከቤተ-መቅደስ ወጥታ፥ "እጮኛዋ" ለተባለው፡ ለዮሴፍ፡ በእጮኛነት ተሰጥታ፡ ከእርሷ በፊት፡ ልጆችን ወልዳለት ከሞተችበት ሚስቱ ቤት ገብታ፡ ገና በዚያ እየኖረች ሣለች፣ 'በኵር' የተባለ ልጇን፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ከመንፈስ ቅዱስ፡ በድንግልና ፀንሳና ዐርግዛ፡ ከወለደችው በኋላ፡ ከዚሁ፡ "እጮኛዋ" ከመባል ካላለፈው፥ የመሲሑ ሕፃንና የእርሷ፡ የእናቱ ጠባቂ ከኾነው፡ ከዮሴፍ ጋር፡ የሩካቤ-ሥጋ ግንኙነት ሳታደርግ፥ ከእርሱም፡ ሌሎች፡ ወንዶችንና ሴቶችን ልጆች ሳትወልድ፡ ከሟችቷ ሚስቱ የወለዳቸውን ልጆቹን ብቻ እያሳደገች፡ በድንግልናዋ ጸንታ ኖራለች!" የሚሉት!?

ነገር ግን፡ ከእነዚሁ፡ የክርስቲያን ወገኖች መካከል፥ በተለይ፡ በእኔ ስም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ተብላችሁ የተጠራችሁት፥ ቀድሞም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" የተባላችሁ፡ እናንተ፡ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ብቻ፡ የእኛን የእግዚአብሔርን እውነት፡ እንዲህ በእምነት አጽንታችሁ፡ ይኸው፡ እስከአኹን በመቀጠላችሁ ምክንያት አይደለም እንዴ! ታዲያ! ይህ፡ የሥርዓቱ ትክክለኛ ይትበሃል፡ እነሆ፡ ዛሬ፡ በእኔ የዐዋጅ ቃል ሊነገር የበቃው!?

ይኸውም፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ "ወንድሞችና እኅቶች" ተብለው፡ በምሥራቹ መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱት የቤተ-ሰቡ አባሎች፡ በእርግጥ፡ እነማን እንደኾኑ ገላልጦ የሚያሳውቀው እውነታ ነው።

አዎን! እነዚህ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ <u>"ወንድሞችና እኅቶች"</u> ተብለው፡ በምሥራቹ መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱት የቤተ-ሰቡ አባሎች፡ *"ድንግል ማርያም፡ ከእጮኛዋ ዮሴፍ የወለደቻቸው ናቸው!"* በማለት፡ እኔም፥ እጮኛዬም፡ ድንግልናችንን አጥተን፡ በቀጥታ፡ ከእርሱ፡ ከዮሴፍ እንደወለድኳቸው አድርገው፡ ይህን ክፉ ነገር ያፈለቁት፥ ይህንም የሓሰት ይትበሃል የመሠረቱት፡ የሓሰቱ አባት ዲያብሎስና ጭፍሮቹ ሓሰተኞች ፍጡሮቻችን ናቸው።

ቀደም ብዬ የጠቀስኳቸው፡ እነዚያ ክፉዎች ሰዎች፡ መቸም፡ የምሕረታችን ዋስትና ስለማይለያቸው ይድናሉ እንጂ፡ እውነቱ፡ እነርሱ፡ በምትሓት እንዳሰቡትና እንደሚያስቡት፥ እንደተናገሩትና እንደሚናገሩት፥ እንደጻፉትና እንደሚጽፉት፥ እንዳደረጉትና እንደሚያደርጉት አለመኾኑን፡ እናንተው፡ በቅዱሱ ኪዳን ርትዕት ሃይማኖታችሁ እያጠራችሁ፡ ልታስተካክሉት ይገባችኋል።

እኔ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ጥንት፡ ከፍጥረት አስቀድሞ፡ በመጀመሪያ፡ በመለኮትነት፥ ኋላም፡ ከፍጥረት ቀጥሎ፡ በመጨረሻ፡ በትስብእትነት [በሰውነት]፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ በድንግልና ከወለድሁት፡ ከመጀመሪያውም፥ ከመጨረሻውም፡ ከአንዱ፡ ከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ በቀር፡ ከድንግላዊው እጮኛዬ፡ ከጻድቁ ዮሴፍ የወለድሁት፡ አንድም ሌላ ልጅ እንደሌለኝ፡ እኔ፡ በእግዝእተብሔር እም'ነቴና በድንግል ማርያምነቴ የማውቀውን ያህል፡ እናንተም፡ የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ ታውቁታላችሁ። የመለኮትነት እና የትስብእትነት ድንግልናዬና ሙሽርነቴ፥ እናትነቴና እኅትነቴ፡ የዘለዓለም ነው።

እንደዚሁም፡ እነዚሁ፡ የልጄ የወዳጄ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ <u>"ወንድሞችና እኅቶች"</u> ተብለው፡ በምሥራቹ መጻሕፍት ውስጥ የተጠቀሱት የቤተ-ሰቡ አባሎች፡ "እጮኛዬ" የተባለው ዮሴፍ፡ "ከቀደመችው ሚች ሚስቱ የወለዳቸው ልጆቹ ናቸው!" የሚባለው ይትበሃል፡ የሓሰት አባት የኾነው ዲያብሎስና ጭፍሮቹ ሓሰተኞች ፍጡሮች ያፈለቁት የሓሰት ይትበሃል እንጂ፡ "ከቀደመችው ሚች ሚስቱ የወለዳቸው ልጆቹ" አይደሉም፤ የሉትምና።

በመሠረቱ፡ ጻድቁ ዮሴፍ፡ ለእኔ ካለው፡ ከንጹሑና ከቅዱሱ አፍኣዊ እጮኛነቱ፥ ከተፈጥሮ ጃንደረብነቱና ከድንግልናዊ ብቅዓቱ የተነሣ፡ ጥንቱኑም፡ ሚስት አላገባም። ሚስት ሊያገባም አይቻለውም። ሚስት የለውም። ስለዚህ፡ ጻድቁ ዮሴፍ፡ አንድም ልጅ የለውም፤ አልወለደም። ለእኔ ያለው፡ አፍኣዊ እጮኛነቱና ጻድቅነቱ፥ ጃንደረብነቱና ድንግላዊነቱ፡ በእውን የታወቀውና የተረጋገጠው፡ በዚህ እግዚአብሔራዊ እውነታ ነው።

ነገር ግን፡ እኛ ኹለታችን፡ ገና በድንግልና፥ በእጮኛነትና በሙሽርነት እያለን ጀምሮ፣ ክፉዎች አይሁድን፡ ከክፋታቸው ለማገድ፥ እኔን እግዝእተብሔር ድንግል ማርያምን እና እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ ከፅንሰት ጀምሮ፡ ከዚያ የከፋት ጭካኔያቸው ለመጠበቅ ሲባል ብቻ፡ በባልና ሚስትነት የትዳር ኑሮ እንዳለን ማስመሰል መልካምና አግባብ ኾነ።

በኹለታችንም እጮኛሞች በኩል፡ የተቀበልናቸውን፡ የወንድምና የእኅት፥ የአጎትና የአክስት፥ የሌሎችም ዘመዶችና ወገኖች፡ ሙታን ልጆችን፥ ማደጎዎችንም፡ እኔ፡ ድንግል ማርያም፡ በእናትነት፥ እንዲሁም፡ ድንግላዊው እጮኛዬ፡ ጻድቁ ዮሴፍ፡ በአባትነት፥ ሕፃን ልጄን፡ ኢየሱስ መሲሕንም፡ እንደአንድ ሕፃን ልጃችን በማየት፡ ለእኛ፡ በልጅነት፣ ለእነርሱ ግን፡ በወንድምነት፡ ከሕፃንነታቸው ጀምረን፡ እንደልጆቻችን አድርገን፡ ከሕፃን ልጄ፡ ከኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ በማደጎነት ያሳደግናቸው ናቸው። ይህ ነው፡ እውነተኛው ይትበሃል።

ይህ እውነተኛ ይትበሃል፡ በቅዳሴ ማርያም ጸሎታችሁ ውስጥ፡ "**ወያዕቆብ ሓዋርያ፡ እኁሁ ለእግዚእነ፡ ኤጲስ ቆጶስ፡ ዘኢየሩሳሌም!**" የሚለውን አንቀጽ፡ "በኢየሩሳሌም፡ ኤጲስ-ቆጶስነትን ስለተሾመ፡ የጌታችን ወንድም ስለሚኾን፥ ወንጌልን ዞሮ ስላስተማረ፡ ስለያዕቆብ ብለህ! አንድም፡ በእርሱ አማላጅነት!" ብላችሁ፡ በነጠላው ከተረጐማችሁት በኋላ፡ በትርጓሜ አንድምታችሁ ስታትቱት፡ "መገናኛው ጕንዱ፡ አልዓዛር ነው። አልዓዛር፡ ቅስራንና ማትያንን ይወልዳል። ቅስራ፡ ኢያቄምን፣ ኢያቄም፡ እመቤታችንን [ቅድስት ድንግል ማርያምን]፣ እመቤታችን፡ ጌታን [ኢየሱስ መሲሕን]። ማትያን፡ ያዕቆብን፣ ያዕቆብ፡ ዮሴፍን፣ ዮሴፍ ያዕቆብን ይወልዳል።

"በአንፃር ያለ ነውና፡ 'እኁሁ [ለእግዚእነ!]' አለ። ለተዘምዶውስ፡ [ለኢየሱስ መሲሕ]፡ 'እነያዕቆብ፥ እነዮሓንስ ወልደ-ዘብዴዎስ ይቀርቡታል!' ብሎ፡ [ድንግል ማርያም፡ ያዕቆብን]፡ እናቱ፡ በሕፃንነቱ ሙታ፡ ከአባቱ [ከዮሴፍ] ቤት አግኝታው፡ ከጌታ [ከሕፃኑ ኢየሱስ] ጋራ እያጠባች አሳድጋዋለችና። "ሐሊብ ድንግልናዊንስ [ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የተዘጋጀ የድንግል ማርያምን የጡት ወተት]፡ ዕሩቅ ብእሲ [ተራ ሰው] ለመጥባት አይቻለውም!" ብሎ፡ እንደእናት አሳድጋዋለችና።" በሚል ቃል ተጽፎ ይነበባል።

ይህን ውስብስብና አስቸጋሪ ኹኔታ፡ በበለጠ ያባባሰውንና ያማሰነውን፡ ዋናውን የጠንቁን ምንጭ ደግሞ፡ ይኸውላችሁ! ስሙት! ይኸውም፡ በዓርብ ውዳሴ ማርያም ጸሎታችሁ ውስጥ፡ "**ማርያም ድንግል፡ ትጸርሕ በቤተ-መቅደስ። ወትብል፡- 'የአምር እግዚአብሔር፣ ከመ አልብየ፡ ዘአአምር ባዕደ፤ ወኢምንትኒ፡ ዘእንበለ ድምፀ-ቃሉ ለመልአክ፡ ዘአብሠረኒ በክብር፤ ወይቤለኒ፡- ‹ሰላም ለኪ! አ ቅድስት ድንግል።**

"ድንግል ማርያም፡ በቤተ-መቅደስ ተናገረች። እንዲህም አለች፡- ‹'ምልዕተ ክብር ሆይ! እግዚአብሔር፡ ከሥጋሽ፡ ሥጋን፥ ከነፍስሽም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ አንድ አካል ይኾናል!' ብሎ፡ መልአኩ፡ አክብሮ ከነገረኝ ነገር በቀር፡ ምን ምን የማውቀው እንደሌለኝ፡ እግዚአብሔር ያውቃል!› ብላ ተናገረች።" ብላችሁ፡ በነጠላው ከተረጐማችሁት በኋላ፡ ታሪኩን፡ በትርጓሜ አንድምታችሁ፡ እንዲህ ስትሉ አትታችሁታል፡-

"እመቤታችን [ቅድስት ድንግል ማርያም]፡ የብፅዓት ልጅ ናት። ሦስት ዓመት ሲኾናት፡ እናት አባቷ፡ ወስደው፡ ለካህናት ሰጥተዋታል። ካህናትም፡ ከቤተ-መቅደስ አገቧት። በቤተ-መቅደስ፡ ዐሥራ-ኹለት ዓመት ትኖራለች። ይህ ዐሥራ-ኹለት ዓመት፣ ካባት ከናቷ ቤት፡ ሦስት ዓመት፣ [ሲደመር፡] ዐሥራ-አምስት ዓመት ይኾናል።

"[ቅድስት ድንግል ማርያም] ዐሥራ-አምስት ዓመት ሲኾናት፡ አይሁድ፡ 'ናሁ ወርዘወት፡ ወለተ-እስራኤል! መጠነ-አንስት አደረሰች፤ ቤተ-መቅደስ ታሳድፍብናለችና፡ ትውጣልን!" አሉ።

"[ካህኑ] ዘካርያስ ገብቶ፡ 'እንደምን ትኾኚ?' ብሎ ቢጠይቃት፤ 'ወደእግዚአብሔር አመልክትልኝ እንጂ፡ እኔ፡ ምን አውቃለሁ!?' አለችው።

"ወደእግዚአብሔር ቢያመለክት፡ 'ከነገደ ይሁዳ፡ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን አስቈጥረህ፡ ብትራቸውን፡ ከቤተ-መቅደስ አግብተህ፡ አውጣ!' አለው።

"ብትራቸውን ሰብስቦ፣ ከቤተ-መቅደስ አግብቶ፡ ቢያወጣው፣ ከበትረ-ዮሴፍ [ከዮሴፍ በትር] ላይ፡ 'አ ዮሴፍ፡ ወልደ-ዳዊት! ኢትፍራህ ነሚኦታ፡ ለማርያም ፍኅርትከ! የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ! እጮኛህን ማርያምን መውሰድን አትፍራ!' የሚል ቃል ተቀርፖ ተገኝቷል፤ ርግብም ወርዳ፡ ከራሱ ላይ ዐርፋበታለች፤ ዕፃም ቢጣጣሉ፡ ለእርሱ ደርሳዋለች።

"'በዚያም፣ በዚያም ኾነ፡ እንካ! ካላሰናበትንህ አትንካ!' ብለው ሰጡት። ከዚህ በኋላ፡ ከቤቱ ወስዶ አኖራት።

"ጊዜው፡ ዓጸባ [ችጋር] ነበርና፡ ዮሴፍ፡ ንግድ ኼዶ፡ ሦስት ወር ኖሮ ቢመለስ፡ 'ዮሓንስ' የሚባል፡ ፈላስፋ ወዳጅ ነበረው፡ ሊጠይቀው መጣ። ተጫውተው ሲሸኘው፡ ፈላስፋ ነውና፡ በመልኳ ዐውቆ፡ 'ይህች ብላቴና ፀንሳለች፤ ካንተ ነው? ከሌላ?' አለው።

"'እኔስ፡ እንኳን የገቢር፣ የኀልዮ አላውቅባትም!' አለው።

"'እንኪያስ፡ ገብተህ ጠይቃት!' አለው።

"ዮሴፍ፡ ወደእርሷ ገብቶ፡ 'አ ወለተ-እስራኤል! መኑ ቀረፀ፡ አክናፈ ድንግልናኪ? አንቺ፡ የእስራኤል-ልጅ ሆይ! ድንግልናሽን ማን ገሠሠው?' ቢላት፣

"'እኔስ፡ መልአኩ፡ አክብሮ ከነገረኝ በቀር፡ ሌላ አላውቅም!' ብላ ተናግራ ነበርና፡ 'ፀርሐት' አለ።"

## የድንግል ማርያም እጮኛ፡ የጻድቁ ዮሴፍ፡
## ጃንደረብነት እና ድንግላዊነት።

እንግዴህ፡ በማስተዋል ተመልከቱት! ያን የመሰለ፡ እግዚአብሔራዊ የመተጫጨት ሥርዓት እያለ፥ ያም ሥርዓት በአግባቡና በይፋ ተፈጽሞ፥ መለኮታዊው እና ትስብእታዊው፥ መንፈሳዊው እና ቅዱሱ ትዳር፡ "እጮኛ" በሚለው መታወቂያ ስያሜ ተጀምሮ የቀጠለ ሲኾን፣ እንደዚያ ያለ፡ ከፍተኛ ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥል፡ የፍልስፍና ጥያቄን ያስከተለ፣ ውስብስብ ችግር እንዲከሠት ማድረጉ፡ ለምን አስፈለገ? ለምንስ እንደሚበጅ ታሰበ?

አዎን! እኛ እግዚአብሔር፡ ለዚህ፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ ታላቅና ልዩ ዓላማ፡ ከግብ መድረስ፡ ለኛ ብቻ ሳይኾን፡ ለሰዎች ፍጡሮቻችን ጭምር፡ "መልካምና ፍሬያማ፥ አስፈላጊና ተገቢ ነው!" ብለን የሠራነው፡ የጠራና የቀና፡ ሥርዓት እያለ፥ ያም ሥርዓት፡ ፍሬያማ ኾኖ፡ እየተሠራበት ሲኖር እየታየ፡ ይህን ትቶ፥ ወይም፡ እንደሌለ በመቍጠር፡ እንዴት፥ ለምንስ፡ ባዕድ የኾነ፡ ያን የመሰለ፡ የተቃወሰ አካኼድንና አሠራርን የያዘ መንገድ ሊከፈት ተቻለ!?

ለዚህ፡ የአንድ ጊዜ ብቸኛና ብርቅ ተልእኮ [አገልግሎት]፡ እንደሌሎቹ ኹሉ፡ ራሱን የሚያበቃ፥ እኛም፡ በእግዚአብሔርነታችን እንደሚበቃ ዐውቀን የምንመርጠውና የምናዘጋጀው፥ የምንጠራውና የምንመድበው፡ ፍጹም ሰው እንደሚኖር የታወቀና የታመነ ሲኾን፡ እንዴት፡ "ኑፋቄ" የሚባለውን የጥርጣሬ ማዕበል፥ ወይም፡ ያን የመሰለ የሃይማኖት ውዝግብን፡ በቀላሉ ጋብዞ፡ ልጆቻችንን ሲያተራምስና ሲለያይ፥ ሲያጣላና እስከደም መፋሰስ ያደረሰ ጠንቀኛ አስተሳሰብን ሲዘራ የሚኖር ችግርን መሠንቀር ለምን አስፈለገ?

መቼውንም ቢኾን፡ የእኔ፥ የልጄም ተቃዋሚዎችና አሳዳጆች የኾኑት አይሁድ፡ ከመጀመሪያው አንሥተው፡ ለእኛ አያርፉምና፡ ገና፡ በቤተ-መቅደስ ሣለሁ፡ በዕድሜዬ ፲፫ ዓመት ኾኖኝ፡ ለዓቅመ ሔዋን ስበቃ፡ በዚያው በክፉው አሳባቸው፡ "ይህች ልጅ፡ አካለ-መጠነ-አንስት ስላደረሰች፡ ቤተ-መቅደሳችንን ታሳድፍብናለችና፡ ትውጣልን!" ብለው፡ የሓሜት ስሞታንና የክስ አቤቱታን፡ በእኔ ላይ ባቀረቡብኝ ጊዜ፡ ካህኑ ዘመዴ፡ ዘካርያስ፡ ወደእኔ ገብቶ፡ "እንደምን ትኾኚ?" ብሎ ቢጠይቀኝ፡ "ወደእግዚአብሔር አመልክትልኝ እንጂ፡ እኔ፡ ምን አውቃለሁ!?" ብዬ የሰጠሁትን መልሴን ተከትሎ፡ ወደእግዚአብሔር ላመለከተልኝ አቤቱታዬ፡ ያገኘሁት፡ አምላካዊ መልስ፡ *"'‹ከነገደ ይሁዳ፡ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን አስቈጥረህ፡ ብትራቸውን፡ ከቤተ-መቅደስ አግብተህ፡ አውጣ!›አለው።'* የሚል ነው!" ተባለ።

ይኾን እንጂ፡ እግዚአብሔራዊው ምላሽ፡ በእርግጥ፡ ይህ ነበርን? እንዳልኾነማ፡ እናንተ የኢትዮጵያ ልጆቼ ታውቁታላችሁ። እንዴትስ፡ ሊኾን ይችላል? ቀደም ብዬ በገለጽኋቸው ምክንያቶች፡ ሊኾን አይችልም። ይህማ፡ ሌላው ሓሳዊው ይትበሃል ነው።

ይህ ሓሳዊ ይትበሃል፡ የእናንተ የኢትዮጵያ ልጆቼ ሳይኾን፡ ያው፡ እንደለመዱትና እንዳስለመዱት፡ የሓሰት አባታቸው በኾነው፡ በዲያብሎስ የሚመሩት፡ የኦሪታውያኑ አይሁድና የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መነኮሳት ስሑት [የሓሰት] አስተምህሮ ያስከተለው፡ የድፍረትና የማሳሳት ግብራቸው መራራ ፍሬ ነው። በመኾኑም፡ እናንተ፡ የዛሬዎቹ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ እንደቀደሙት ታማኞች ምዝላቶቻችሁ ልጆቼ ኹሉ፡ የዚህን ቍም-ነገር እውነታ፡ ከዚህ የዐዋጅ ቃሌ ተረድታችሁትና ተገንዝባችሁት፡ ይህን የተሳሳተ ይትበሃል፡ በእግዚአብሔርዋ እውነት፡ ዐርማችሁ የምታስተካክሉት ይኾናል።

የእኛ በኾነችው፡ እኛ በምንመራትና በምንጠብቃት **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥታችን*** ዘንድ፡ ከእኛ እውነት ጋር የማይስማማ፡ ስሑት [የሓሰት] ይትበሃል፡ በምንም መልኩና ይዘቱ፡ እስከዛሬም የለም፤ እንዲኖር ሊያደርጉ የሞከሩ ቢኖሩም፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ሊኖርና ሊሠራ፥ በህልውናውም ሊቀጥል ፈጽሞ አይቻለውም።

ስለዚህ፡ ለእኔ፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም "እጮኛ" የተባለውን፥ ደግሞም፡ ለሕፃኑ ልጄ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ እና ለእኔ ለእናቱም፡ አገልጋይ የኾነውን፡ ጻድቁ ዮሴፍን በሚመለከት፣ ይህ የዐዋጅ ቃሌ፡ እንዲህ በይፋ እንዲወጣላችሁ የተደረገው፡ ከዚህ አስቀድሜ ዘርዝሬ በገለጽሁላችሁና ከዚህ አስከትዬ በምገልጻቸው እውነቶች ላይ በመመሥረት ነው። እነዚህም፦

፩ኛ. ጻድቁ ዮሴፍ፡ ለእኔ አፍኣዊ እጮኛነት፥ ለሕፃን ልጄና ለእኔ፡ ለእናቱ የአገልጋይነት ተልእኮም፡ ራሱን ያበቃው፥ ከዚህ የተነሣም፡ በእኛ ተመርጦ፡ ለዚሁ ተልእኮ የተጠራው <u>በፍጹም ንጽሕናውና ድንግልናው</u> መኾኑን፥ በዚሁ ንጹሕ ድንግልናው ጸንቶ በመገኘቱም መኾኑን፣

፪ኛ. የጻድቁ ዮሴፍ፡ የድንግልናው አማናዊነትና ፍጹምነት የተረጋገጠው፥ ለዚህ ታላቅና ልዩ አገልግሎት፡ ጥንቱኑም በእኛ፡ የተጠራና ለዚሁ ተልእኮ የተዘጋጀ መኾኑ እንዲታወቅና እንዲከሠት ባደረግንበት፡ <u>የተፈጥሮ ጃንደረባነቱ</u> መኾኑን፣

፫ኛ. አንዲት ሴት፡ ለእግዚአብሔራዊው ሥርዓተ-ጋብቻ የምትታጨው፡ በድንግልናዋ እያለች እንደመኾኑ መጠን፡ እንዲሁ፡ ወንዱም፡ እንደእርሷው ኹሉ፡ <u>እርሱም፡ ድንግል መኾን እንዳለበት</u> የማያጠያይቅ መኾኑን፣

፬ኛ. <u>የመተጫጨትና የእጮኛነት ሥርዓት የሚወጠነውና የሚካኼደው፥ የሚፈጸመውም፡ በአንዲት ድንግሊት ሴት እና በአንድ ድንግል ወንድ መካከል እንጂ፣</u> በአንድ መዓስብ [በፈት፥ ወይም፡ ልጆችን የወለደች ሚስቱ በሞተችበት፡ በአንድ ወንድ] እና በአንዲት ድንግሊት ሴት መካከል አለመኾኑን፣

፭ኛ. እኔ ድንግል ማርያም፥ ድንግላዊው እጮኛዬ ዮሴፍም፡ እውነተኞቹ የመልከ-ጼዴቅ ልጆች የኾንን፡ እኔ፡ ፍጹሟ ኢትዮጵያ፥ እርሱም፡ ፍጹም ኢትዮጵያዊ በመኾኑ፡ የእግዚአብሔር የኾነው ሥርዓተ-ኢትዮጵያ ኹሉ ፈጻሚዎች መኾናችንን፣

፯ኛ. ቀድሞውኑም ቢኾን፡ ለባልና ሚስትነቱ ጋብቻ፡ የመተጫጨቱ ሥርዓት፥ እንዲሁም፡ "እጮኛ" የሚለው፡ የአፍኣ ስያሜ የተፈለገው፥ በተግባርም ላይ እንዲውል የተደረገው፡ የእኔን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን እና የሕፃን ልጄን ወዳጄን፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ማንነት፡ ፍጡሮቻችን ሰዎች፥ በተለይም፡ አይሁድ፡ በምንም መንገድ፡ እንዳይጠረጥሩ ለማድረግ መኾኑን፤

፰ኛ. ከሕፃኑ ልጄ፡ ከእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ፡ ዐብረውት እንዲያድጉ የተደረጉትን፤ በእኔ እና በአፍኣ እጮኛዬ፡ በዮሴፍ በኩል ያሉ፡ የሕያዋንና የሙታን ወንድምና እኅት፥ አጎትና አክስት፥ ዘመዶችና ችግረኞች፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን፡ ለሕፃን ልጄ ወዳጄ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንደወንድሞችና እኅቶች፥ ለእኛም፡ እንደራሳችን ልጆች አድርገን ማሳደጋችን፡ ይህንኑ፡ የማንነታችንን ሥውር ሽፋን፡ በበለጠ ማጠናከራችንና ማጉላታችን መኾኑን፡ በበለጠ የሚያሳውቁና የሚያስተማምኑ፥ የሚያረጋግጡም ናቸው።

ከዚህም ጋር፡ ከጥንት ጀምሮ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዙፋን ላይ የተቀመጡት፡ ከእኔ በፊት፡ ማክዳን፥ ከእኔ በኋላ ደግሞ፡ ሕንደኬን የመሰሉት፡ አያቶቼ እና የልጅ-ልጆቼ ደናግል አጼዪያት [ንግሥታት]፡ በድንግልናቸው እንደጸኑ ኾነው፡ ሕዝባቸውን በሚመሩበትና በሚጠብቁበት ጊዜ፡ ኢትዮጵያዊዉን የብሉይ ኪዳን አቤሜሌክን እና ኢትዮጵያዊዉን የአዲስ ኪዳን አቤሜሌክን [ባኮስን]፡ ጃንደረቦቻቸው አድርገው ያስቀመጡበት፡ የሥርዓተ-መንግሥት ልማድና ሥርዓት እንዳለ፡ ልታዘክሩትና ልትገነዘቡት ይገባችኋል።

የፍጻሜ ሕይወት ዘመን ደርሶ፡ እኔም፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ በጊዜው፡ በንግሥናው ዙፋን ላይ፡ በንግሥትነት ስቀመጥ፡ በፍጥረት ዜና መዋዕል ውስጥ፡ ፍጹም ልዩ እና ታላቅ ለኾነ፡ ለዚህ የታማኝነትና የባለአደራነት ተልእኮ [አገልግሎት] የጠራኹትን፤ ጻድቁ ዮሴፍን፡ በ"አፍኣዊ እጮኛ" ስም፡ <u>ጃንደረባዬ</u> አድርጌ የተቀበልሁትና የመደብሁት፥ እርሱም ገናና የኾነ፡ ይህን የተቀደሰ፡ <u>የጃንደረብነት አገልግሎቱን የፈጸመው፡</u> በዚሁ መንግሥታዊ በኾነው፡ ሕያው ልማድና ሥርዓት መሠረት መኾኑን፡ ዛሬ የማሳውቃችሁ፡ በዚሁ የእናትነትና የንግሥትነት ፍቅሬ፡ በእናንተ ልጆቼ ላይ ያሳደርሁትን፡ የደስታ በረከት እያበዛሁላችሁ ነው።

## መፈጽም።

እንግዲህ፡ በአብርሃም-ግዝረት የከፈትሁትንና በሕፃን ኢየሱስ የሕጽወት-ግርዛት ያማከልሁትን የዐዋጅ ቃሌን፡ በዮሴፍ የጃንደረብነት ድንግልና እፈጽመዋለሁ።

"የድንግል ማርያም እጮኛ" ሲባል፡ ለዝንተ-ዓለም የኖረውና ወደፊትም፡ በዚሁ አጠራር ሲጠቀስ የሚኖረው፡ ጻድቁ ዮሴፍ፡ የኢትዮጵያዊዉን መልከ-ጼዴቅ የሕይወት ፈለግ ተከትሎ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥ ነጋሢና ካህን ኾኖ በቤተ-መቅደስ እያገለገለ ይኖር የነበረ ጐልማሳ ነው።

በሰውነቱ፡ ለዓቅመ አዳም የዕድሜ ክልል በደረሰ ጊዜ፥ በተፈጥሮው ሕፅው [ጃንደረባ]፥ በባሕርዩም፡ ድንግል ኾኖ፥ ራሱንም ለዚሁ ማዕርግ አብቅቶ በመገኘቱ፡ ለእኔ፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ አፍኣዊ እጮኛነት፥ ለልጇ ለወዳጇ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ሕፃንነት እና ለእኔም፡ እናትነት አገልጋይነት ተጠራ።

እንዲህ፡ በእኔ፡ በኢትዮጵያነቴና በአጼዩት ንግሥትነቴ፡ እንደማናቸውም የኢትዮጵያውያት ደናግል ንግሥታት ጃንደረቦች ሁሉ፡ እርሱ፡ ጻድቁ ዮሴፍም፡ በምድር ላይ፥ በሰዎች መካከል፡ የእኔ፡ የንግሥት እናቲቱ፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ጃንደረባ እና የሕፃን ንጉሡ ልጇ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ባለሟል ባልደረባ ኾነ!

ጻድቁ ዮሴፍ፡ ከሌሎቹ ኹሉ የሚለይበትና የሚልቅበት ጸጋ ቢኖር፣ ከዚህ የተነሣም የተቀዳጀው ልዩ ክብር ቢኖር፡ በአንድ በኩል፡ ለእኔ እጮኛነት ያበቃው ድንግልናውና ጃንደረባነቱ ሲኾን፣ በሌላው በኩል ደግሞ፡ የልጇ የወዳጇ የሕፃንነቱና የእኔ የእናትነቴ አገልጋይ ለመኾን መታደሉ ነው።

ጻድቂት ሰሎሜም፡ እንደጻድቁ ዮሴፍ ኹሉ፡ እርሷም፡ በድንግልናዋ፡ ራሷን፡ ለዚህ ልዩ እና ታላቅ አገልግሎት ያበቃች ኾና ስለተገኘች፤ እኛ እግዚአብሔር፡ ለዚሁ፡ የጻድቁ ዮሴፍን ለሚመስለው፥ ለእርሷ ዕድል ፈንታ ለሚመጥነው ጸጋና ክብር፡ የመረጥናትና የጠራናት፥ የመደብናትም ኢትዮጵያዊት ልጃችን ናት።

"ጃን"፡ በኢትዮጵያኛ፣ "ጃን-ሆይ! ጃን-ሜዳ፣ ጃን-ጥላ" እንደሚባለው፣ "ንጉሥ/ንግሥት" ማለት መኾኑን፣

ጃን-ደረብነት፡ የንጉሥ/የንግሥት፡ የቅርብ ጓደኛነትንና ባለሟልነትን የሚያመለክት ትርጉም ያለው ስያሜ ሲኾን፣ "የባል-ያህል ቅርበት ያለው!" ለማለት ደግሞ፡ "ባል-ደረባ" የሚለውም ቃል፡ ከዚሁ፡ "ጃን-ደረባ" ከሚለው ቃል ጋር፡ የትርጉም አግባብነት ባሕርይ ያለው መኾኑን ልታጤኑት የሚያስፈልጋችሁ ይኾናል።

\+ + +

**ተዐውደ፡ በመስከረም ፲፯ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።**

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።

\+ + +